# <u>ጥናት አንድ ኤፌ 1፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. መልዕክቱን የጻፈው ሰው ጳውሎስ ነው፡፡ መልዕክቱ የተጻፈላቸው ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ እንዳሉ፣ የታመኑ እንደሆኑ፣ በኤፌሶን ከተማ እንደሚገኙና፣ ቅዱሳን እንደሆኑ ጸሐፊው ይናገራል፡፡ የጸጋና የሰላም ምንጭ እንደሆነ በዚህ ክፍል ውስጥ የተነገረለት እግዚአብሄር አብና እግዚአብሄር ወልድ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡
2. ጳውሎስ እግዚአብሄርን የሚባርክበት ምክንያት በበረከቱ ስለባረከን ነው፡፡ 1) ‹‹በሰማያዊ ሥፍራ›› የበረከቱን ሥፍራ 2) ‹‹መንፈሳዊ በረከት›› የበረከቱን ዓይነት 3) ‹‹ሁሉ›› የበረከቱን መጠን 4) ‹‹በክርስቶስ የባረከን›› በረከቱ የመጣበትን መንገድ 5) ‹‹የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት›› የበረከቱን ሰጪ ማንነት ያስረዱናል፡፡
3. የተመረጥነው በፊቱ ቅዱሳንና ነውር አልባ እንድንሆን ነው፡፡ የተመረጥነው በማናቸውም በተዘረዘሩት ምክንያቶች እንዳልሆነ የምንረዳው፣ ምርጫው የተካሄደው ገና ከእናታችን ማህጸን ውስጥ ሳንወጣ ማለትም አለም ከመፈጠሩ አንስቶ ስለሚል ምክንያቶቻችንን ሁሉ ባዶ ያደርጋቸዋል ማለት ነው፤፤ የእግዚአብሄር ምርጫ የመጣበትም መንገድ እርሱ በማለት በሚናገርለት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እንደሆነ ይነግረናል፡፡
4. ሌላው በክርስቶስ በኩል የተደረገልን ነገር የእግዚአብሄር ልጆች እንድንሆን መወሰኑ ነው፡፡ እግዚአብሄር አምላክ ይህንን ዓይነት በጎነት ሊያደርግልን ያነሳሳው ነገር በቁ6 ላይ እንደምናነበው እንዲሁ በነጻ እንደሆነና ይህ በነጻ ያደረገውም ይህ ክቡር የሆነው ጸጋው እንዲመሰገን ነው በማለት ይናገራል፡፡
5. በደሙ የተደረገ ቤዛነት፣ የሃጥያት ይቅርታ ተሰጠን፣ ጸጋውን በጥበብና በማስተዋል ሁሉ አበዛልን፣ የፈቃዱን ምስጢር እንደ በጎ ሃሳቡ እንድናውቅ አደረገ፡፡ ይቅርታ ማግኘት የቻልነው በ2ኛ ቆሮ 5፡21 ላይ እንደሚናገረው እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሄርን ይቅርታ ተቀብለን ጻድቃን እንድንሆን፤ ሃጥያት ያላወቀውን ልጁን ኢየሱስ ስለእኛ ሃጥያት በመስቀል እንዲሰቃይና እንዲሞት በመፍቀድ ነው፡፡
6. ቁ10 ላይ እንደምናነበው የእግዚአብሄር የወደፊት ዕቅድ በሰማይና በምድር ያሉትን ነገሮች ሁሉ ጠቅልሎ በክርስቶስ ስር ማስገዛት ነው፡፡ ይህ ስም ትልቅ ቦታ የተሰጠው ምክንያት በሐዋ ሥራ 4፡12 ላይ እንደተነገረን ደህንነት ሌላ በማንም እንደማይገኝና ሰዎች ሁሉ ይድኑበት ዘንድ ከሰማይ በታች የተሰጠ ስም ከኢየሱስ በስተቀር የለምና ነው፤ ለዚህም ነው ሰማያዊ በረከታችንን ሁሉ መቀበል የምንችለው በእርሱ በኩል ብቻ ነው፡፡
7. የክርስቶስ ወገን ለመባል ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የተነገረው ነገር የእውነትን ቃል ማለትም የደህንነትን ወንጌል ሰምቶ ማመን ነው፡፡ በክርስቶስ ያመነ ሰው ቁ13 እንደሚነግረን እግዚአብሄር በመንፈስ ቅዱስ ማህተም እንዳተመው እናነባለን፡፡
8. በእግዚአብሄር አምላክ በበልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ላመኑት ሁሉ የዘለዓለም ርስትን እንደሚያወርሳቸው ቃል ገብቷል፤ ይህንንም የገባውን ቃል ያላንዳች ጥርጣሬ ተፈጻሚ እንደሚሆን በማያሻማ መንገድ ለማረጋገጥ መንፈስ ቅዱስን መያዣና ዋስትና አድርጎ በውስጣችን እንዲኖር እንደሰጠን ነው እኔ የምረዳው፡፡ ሮሜ 8፡17 ገላ 3፡29 ገላ 4፡7 ኤፌ 3፡6

## ጥናት ሁለት ኤፌ 1፡15-23 ለመሪው የተዘጋጀ

1. በነዚህ ሰዎች ህይወት ውስጥ ተገልጠው የምናያቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው በጌታ ኢየሱስ ያላቸው እምነት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ለቅዱሳን ሁሉ ያላቸው ፍቅር ነው፡፡ ጳውሎስ ለነዚህ ሰዎች እያደረገ ያለው ነገር በጸሎት በእግዚአብሄር ፊት ማስታወስና ስለእነርሱ ደግሞ እግዚአብሄርን ሳያቋርጥ ማመስገን ነው፡፡
2. አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በኢየሱስ አምኛለሁ ወይም ክርስትያን ነኝ በማለት በአፋቸው እየተናገሩ ነገር ግን የእግዚአብሄር ቤተሰቦች ከሆኑት ከቅዱሳኑ ጋራ በፍቅር የመኖርን ነገር እንደ አስፈላጊ ነገር አያዩትም፤ ነገር ግን የእምነታችን ትክክለኛነት ትልቅ መመዘኛ ሊሆን የሚችለው ነገር እግዚአብሄር አባታችን ከሆነ የእርሱን ልጆች ደግሞ ማፍቀር ግዴታችን ነው፡፡ ለዚህም 1ኛ ዮሐ 5፡1-2 ማንበብ ይረዳል፡፡
3. ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቅዱሳነ የሚጸልየው የሌላቸው ነገር እንዲሰያቸው ሳይሆን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ የተሰጣቸውን ታላቅ በረከት እንዲያውቁና እግዚአብሄር አይናቸውን ከፍቶላቸው ማየት እንዲችሉ ነው፡፡
4. በኤፌ 1፡1-14 ላይ ከእግዚአብሄር የተቀበልናቸውን የበረከት ዓይነቶች በዝርዝር የነገረን ሲሆን፤ በቆሮንቶስ ላይ 2፡10-15ትን ስናነብ ማናቸውንም መንፈሳዊ እውነት ለመረዳት የእግዚአብሄር መንፈስ ሊገልጥልን ያስፈልጋል፤ ስለሆነም ነው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ውስጥ ለኤፌሶን ቅዱሳን የመገለጥን መንፈስ እንዲቀበሉ የጸለየው፡፡
5. እነዚህ ሰዎች እነዚህን ሶስት ነገሮች እንዲረዱና እንዲያውቁ ጳውሎስ እያደረገ ያለው ነገር ወደ እግዚአብሄር መጸለይ ነው፡፡ ከዚህ ክፍል ልንማር የምንችለው ነገር፣ እኛም ሆንን ማንኛውም ሰው መንፈሳዊ እውነትን መረዳት እንዲችል ከፈለግን ማድረግ የሚገባን ነገር እግዚአብሄር አምላክ የልብ አይኖችን እንዲከፍትና እውነቱን ማየት እንዲችሉ መጸለይ ነው፡፡
6. ቁ20 እንደሚናገረው ይህ ሃይል ግልጽ ሆኖ የታየበት ወቅት ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን አስነስቶ በእግዚአብሄር አብ ቀኝ እንዲቀመጥ ሲያደርገው ነው፡፡ ይህ ድርጊት ከማንኛውም ነገር በላይ የሃይሉን ታላቅነት የሚያሳይበት ምክንያት፤ የሰይጣን መሸነፍ የሚረጋገጥበት፣ የኢየሱስ ድል መንሳት የሚታይበት፣ የሰው ልጆች ደህንነት የሚረጋገጥበት አንድ ነገር ቢኖር ትንሳኤ ስለሆነ ሰይጣን ባለ በሌለ ሃይሉ እንዳይሆን የታገለበት እውነት ስለሆነ ክርስቶስ ያንን ሁሉ ድል አድርጎ ከመቃብር ለመውጣት ያስቻለው የሃይሉ ታላቅነት ነው፡፡
7. ኢየሱስ ከግዛት፣ ከስልጣን፣ ከሃይል፣ ከጌትነትና በአሁኑም ሆነ በሚመጣው ዓለም ካለው ስም በላይ አድርጎ እግዚአብሄር በቀኙ እንዳስቀመጠው እንመለከታለን፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ቁ22 እንደሚነግረን ሀሉን፤ ማለትም ማንኛውም ነገር ሳይቀር ከኢየሱስ እግር በታች እንዳስገዛለት እናነባለን፡፡
8. የሰውነታችን ብልቶች በሙሉ ተገቢውን ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ማንኛቸውንም ዓይነት ትዕዛዝና መረጃ ሁሉ የሚቀበሉት ከራሳችን እንደሆነ ሁሉ፤ ቤተ ክርስትያንም ሙሉ በሙሉ የሚገዛና የሚያዛትና የሚያስተዳድራት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆን አለበት ማለት ነው፡፡

<u>ጥናት ሶስት ኤፌ 2፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በነዚህ ቁጥሮች ላይ የተነገረው ነገር እነጳውሎስንም ጨምሮ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነን ለምንገኝ ሰዎች ሁሉ የተነገረ ነው፤ ይህንንም በቁ1 ‹‹እናንተ›› ቁ3‹‹እኛ ሁላችን›› በማለት ከተናገራቸው ሃሳቦች መረዳት እንችላለን፡፡ ሙታን ነበርን፣ የአለምን ክፉ መንገድ እንከተል ነበር፣ ለእግዚአብሄር በማይታዘዙት ሰዎች ላይ ለሚሰራው መንፈስ እንታዘዝ ነበር፣ የሥጋችንን ምኞት እያረካን መንገዱን እየተከተልን እንኖር ነበር፣ የቁጣ ልጆች ነበርን፡
2. እነዚህ አነጋገሮች የሚጠቁሙን ሁኔታዎቹ ያለፉ፣ የቀድሞ ነገሮች መሆናቸውንና ዛሬ የሚካሄዱ ነገሮች አለመሆናቸውን ይጠቁሙናል? ሰው በሥጋው ቆሞ ሊመላለስና በሰዎች አይን ህያው መስሎ ሊታይ ይችላል፤ ነገር ግን ከእግዚአብሄር ጋራ እርቅ እስካላደረገ ድረስ በመንፈሱ የሞተ፣ ከእግዚአብሄር ጋራ ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው ሰው መሆኑን የሚገልጽ አነጋገር ነው፡፡
3. ዓለም የሚለውን ሃሳብ በቁ2 ላይ፣ ሥጋ የሚለውን ደግሞ በቁ3 ላይ በግልፅ ተጠቅሶ የሚገኝ ሲሆን፣ ሰይጣን የሚባለው ደግሞ በቀጥታ ሰይጣን ተብሎ ባይጻፍም በቁ2 ላይ እሱንቱ በዝርዝር ሰፍሯል፡፡ በክርስቶስ ያላመኑ ሰዎች ዛሬ ስለሚኖሩበት ሁኔታ ይህ ክፍል የሚያስተምረን፤ በክርስቶስ ባመኑት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰራው ሁሉ፣ በእነርሱ ላይ ደግሞ የሚሰራ ሌላ መንፈስ እንዳለ አያለሁ፡፡
4. ይህ በቁ4 ላይ አረፍተ ነገር መጀመሪያ ሆኖ የተቀመጠው ‹‹ነገር ግን›› የሚለው አነጋገር ትልቅ ቃል ሆኖ የሚገኝበት ምክንያት የሁኔታችን መለወጫ፤ ማለትም ከሞት ወደ ህይወተ ለመሸጋገር በር የተከፈተልንን መንገድ የሚያበስርልን የምስራች መሆኑ ትልቅ ቃል ነው፡፡ ሙታንን ወደራሱ ለመሳብ የገፋፉት ባህርያት ቁ4 የምህረቱ ባለጠግነት፣ ቁ4 የፍቅሩ ታላቅነት፣ ቁ7 ቸርነቱ እና የጸጋው ባለጠግነት ናቸው፡፡
5. በክርስቶስ ህያው አደረገን፣ በጸጋው አዳነን፣ ከክርስቶስ ጋራ አስነሳን፣ በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋራ አስቀመጠን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሄር አማኝ ሲመለከት በክርስቶስ ውስጥ እንደሆነ ስለሚያየው፤ ለዚህ ነው እኛ ሞተናል፣ ከሙታን ተነስተናል፣ በሰማያዊ ሥፍራ ተቀምጠናል የሚሉትን አይነት አነጋገሮች የሚናገረው፤ ለዚህ ነው ቆላ 3፡3 ላይ ስናነብ ‹‹ሞታችኋልና፤ ህይወታችሁም ከክርስቶስ ጋራ በእግዚአብሄር ዘንድ ተሰውሯልና›› በማለት የሚናገረው፡፡
6. ከቁ8-9 ስለደህንነታችን የምረዳቸው ነገሮች፤ ደህንነት በእምነት እንደሆነ፣ የዳነው በጸጋ መሆኑን፣ ደህንነት የእግዚአብሄር ስጦታ እንጂ ከእኛ እንዳልሆነ፣ ስለደህንነታችን ትምክህት እንደማንችል እናነባለን፡፡
7. በቆሮንቶስ ውስጥ የምናነበው ክፍል እንደሚነግረን ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሳ ነው›› በማለት በራሳችን ሳይሆን በጌታ እንድንመካ ሲያሳስበን፤ በኤፌሶን 2፡9 ላይም ይህንኑ ተመሳሳይ ሃሳብ በማንሳት በሥራችን ያገኘነው ነገር እንዳልሆነና ስለዚህም ትምክህት የሚያስፈልገው ነገር እንዳልሆነ ያስገነዝበናል፡፡
8. በቁ9 ላይ ‹‹ሥራ›› በመባል የተነገረው ደህንነትን ለማግኘት ተብሎ የሚሰራውን ሥራ የሚጠቁም ሲሆን፤ በቁ10 ላይ የምናየው ‹‹መልካም ሥራ›› በመባል የተነገረው ግን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ከሆንን ወጥንም ደህንነትን ካገኘኝ በኋላ የምንሰራውን ሥራ የሚጠቁም ነው፡፡ በአጭሩ ለመናገር የመጀመሪያው ለመዳን የሚሰራ ሥራ ሲሆን፤ ሁለተኛው ግን ስለዳንን የምንሰራው ነው፡፡

## ጥናት አራት ኤፌ. 2፡11-22 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንዲያስታውሱ የተነገራቸው ነገር፤ ከክርስቶስ ተለይተው እንደነበረ፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቀው እንደነበረ፣ ያለ ተስፋ እንደነበሩ፣ ለኪዳኑ ተስፋ ባዕዳን እንደነበሩና፣ ያለ እግዚአብሄር እንደነበሩ ነው፡፡ ይህንን ማስታወስ የሚረዳው በመጀመሪያ ደረጃ የነበሩበትን የከፋ ሁኔታ በማሰብ አሁን ደግሞ የደረሱበትን አይተው ጌታን እንዲያከብሩ፣ ሌላው ደግሞ እነርሱ በነበሩበት ሁኔታ ዛሬ ለሚገኙት አህዛብ የርህራሄ ልብ እንዲኖራቸውና ወንጌልን እንዲያበስሩ እንደሚሆን እገምታለሁ፡፡
2. እነዚህ አነጋገሮች የሚያረጋግጡልን፤ ‹‹ቀድሞ›› የሚለው የቀድሞ ሁኔታችንን አስከፊነት፤ ‹‹አሁን ግን›› የሚለው ደግሞ ዛሬ በተለየና እጅግ በተሸለ ሁኔታ ውስጥ እንደምንገኝ፤ ‹‹ከእንግዲህ ወዲህ›› የሚለው ደግሞ ከፊታችን እግዚአብሄር ያዘጋጀው መልካም ነገር እንዳለ ያረጋግጥልናል፡፡ እነዚህ ሰዎች ቀድሞ ርቀው የነበሩ ሲሆን፤ ዛሬ ግን በክርስቶስ ደም አማካኝነት ቀርበዋል፡፡
3. ሁለቱ በመባል በዚህ ቁጥር ላይ የተነገረላቸው አይሁድና አህዛብ ናቸው፡፡ በቁ14-15 ውስጥ ክርስቶስ የሰራቸው ስራዎች፤ ሁለቱን አንድ ማድረግ፣ የሚለያየውን የጥል ግድግዳ ማፍረስ፣ ለሁለቱም ሰላማቸው መሆን፣ ህግን ከትዕዛዛቱና ከሥርዓቱ ጋራ በሥጋው መሻር ናቸው፡፡
4. በቁ14-15 ላይ ክርስቶስ ያስታረቀው አህዛብንና አይሁድን ሲሆን፤ በቁ16 ላይ ደግሞ እርቅን ያካሄደው በሰዎችና በእግዚአብሄር መካከል ነው፡፡ ሁለቱን ሰዎች ሲያስታርቅ ቁ15 እንደሚነግረን ዓላማው ከሁለቱ አንድን አዲስ ሰው ፈጥሮ በሁለቱ መሃል ሰላምን ለመመስረት ነው፡፡
5. በክርስቶስ መስቀል እንደተከናወኑ የምናያቸው ሁለት ነገሮች፤ የመጀመሪያው ጥልን እንደገደለ ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ አህዛብንና አይሁድን ከእግዚአብሄር ጋራ ማስታረቅ ነው፡፡ ክርስቶስ በመስቀል መሞቱ በእግዚአብሄርና በሰው መካከል ብቻ ሳይሆን በሰውና በሰው መሃልም ያለውን ጥላቻ ለመግደል ስለሆነ፤ እኛም ጥላቻን አስወግደን በፍቅር መመላለስ እንደሚጠበቅብን እረዳለሁ፡፡
6. ‹‹ያልተገረዙ›› የሚል መጠሪያ ነበራቸው፣ ከክርስቶስ ተለይተው፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቀው፣ ለኪዳኑ ተስፋ ባዕዳን ሆነው፣ ያለተስፋና ያለ እግዚአብሄር ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁሉ ትላልቅ ነገሮች ቢሆኑም እንደዋነኛ የሚታየኝ ያለ እግዚአብሄር መሆናቸውና ከክርስቶስ መለየታቸው ነው፡፡ ለዚህ ሁኔታቸው መፍትሄን ያስገኘላቸው በቁ13 ላይ እንደምንመለከተው ክርስቶስ ሲሆን፤ ይህም የሆነው በሞቱ ማለትም በደሙ አማካኝነት ነው፡፡
7. የአንድ አገር ዜጋ ሆነዋል፣ የእግዚአብሄር ቤተሰብ አባል ናቸው፣ በሐዋርያትና በነቢያት መሰረት ላይ ታንጸዋል፣ እግዚአብሄር በመንፈሱ የሚኖርበት ማደሪያ ለመሆን ከሌሎች ሁሉ ጋራ የሚሰሩ ናቸው፡፡
8. ሮሜ 5፡10 ላይ የእግዚአብሄር ጠላቶች እንደነበርን እናነባለን፡፡ ከጠላትነት እርቅ ማግኘት ብቻውን ለእኛ ትልቅ ነገር ሆኖ ሳለ፤ የጎረቤትነት ወይም የጓደኝነትም ሳይሆን ከልጅነት የቀረበ ግንኙነት የለም፤ ስለዚህም ይህ በእኔ አመለካከት ከሃሳቤና ከአዕምሮዬ ሁሉ በላይ የሆነ ነገር ነው፡፡ በአካባቤዬ የማያቸውና አብሬአቸው ያሉት ቅዱሳን ሁሉ እውነተኛ ወንድምና እህቶቼ አድርጌ ላስባቸውና ልቀበላቸው እንደሚገባኝ ተረድቻለሁ፡፡

# ጥናት አምስት ኤፌ 3፡1-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል ረብሻ የተጀመረበትና ጳውሎስ ችግር ውስጥ የገባበት ምክንያት ወንጌልን እግዚአብሄር በጳውሎስ በኩል ለአህዛብ ሊያስተምር እንደጠራው በመናገሩ ነው፡፡
2. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰው ቃል ‹‹ምስጢር›› የሚለው ነው፡፡ ጳውሎስ የእግዚአብሄርን ምስጢር መረዳት የቻለበት መንገድ፤ ቁ3 ላይ እንደምናነበው በመገለጥ እንደነበረ እናያለን፡፡
3. ‹‹ምስጢር›› በመባል በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተነገረው ነገር ምን እንደሆነ የተነገረው በቁ6 ላይ ሲሆን፤ ሶስቱ አበይት ነገሮች አንደኛው፤ አህዛብ በወንጌል አማካኝነት ከእስራኤል ጋራ አብረው ወራሾች መሆናቸው፤ አብረው ደግሞ የአንዱ የክርስቶስ አካል ብልቶች መሆናቸውና፤ በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ተስፋ አብረው ተካፋይ መሆናቸው ነው፡፡ በሶስቱም ውስጥ የሚገኘው አንድ ቃል ‹‹አብረው›› የሚለው ቃል ነው፡፡
4. የማይመረመረውን የክርስቶስን ባለጠግነት ለአህዛብ መስበክና፤ ላለፉት ዘመናት የተሰወረውን የምስጢር አሰራር ለሁሉም መግለጥ ነው፡፡
5. ወደ እግዚአብሄር መቅረብ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ ነው፡፡ ወደ እርሱ ስንቀርብ አቀራረባችን በነጻነትና በልበ ሙሉነት ሊሆን እንደሚገባውም እንመለከታለን፡፡ አማኝም ሆነ ያላመነ ሰው በህይወት ሲኖር ብዙ የተለያዩ ከባድና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንደሚያልፍ የታወቀ ሲሆን፤ ወደ እግዚአብሄር የመቅረብና ያለበትን ሸክም በእርሱ ትከሻ ላይ የማራገፍ መብት ያለው ሰው ሰላምና እረፍትን ከእርሱ ተቀብሎ የመገላገል ችሎታ ስላለው የታደለ ሰው ነው እላለሁ፡፡
6. በምዕራፍ አንድ ውስጥ የጸለየው ጸሎት እግዚአብሄር የሰጣቸውን በረከት ማየት እንዲችሉ ሲሆን በምዕራፍ ሶስት ውስጥ የጸለየው ደግሞ የጸለየላቸው የተሰጣቸውን በረከት ሁሉ በህይወታቸው እውን ሆኖ መለማመድና መኖር እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳቸው ነው፡፡ (ማለትም አይናቸው እንዲከፈትና፤ ባዩት እንዲኖሩ ሃይል እንዲያገኙ ነው፡፡)
7. የመጀመሪያ ጸሎቱ ያተኮረው በውስጥ ሰውነት ጥንካሬ ላይ ነው፡፡ በውስጥ ሰውነት መጠንከር ማለት ልክ ውጫዊው ሰውነታችንን ለማጠንከር እንደ ምግብ፣ ውሃ፣ ስፖርትና የመሳሰሉትን ለጥንካሬውና ለጤንነቱ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማድረግ ጤነኛና ጠንካራ ሰውነት እንደሚኖረን ሁሉ፤ የውስጥ ሰውነታችን ወይም አዲሱ ሰው ለእድገቱና ለጥንካሬው የሚሆነውን በእግዚአብሄር ቃል፣ በጸሎት፣ ከቅዱሳን ጋራ ህብረት በማድረግ ማጠንከር ነው፡፡ ይህን ሁሉ ማድረግ የሚያስችለውን ሃይል የሚሰጠን መንፈስ ቅዱስ ራሱ ነው፡፡
8. በዚህ ቁጥር ላይ ጳውሎስ የጸለየላቸው የክርስቶስን ፍቅር ስፋት፣ ርዝመት፣ ከፍታና ጥልቀት ከቅዱሳን ሁሉ ጋር የመገንዘብ ሃይል እንዲያገኙ ነው፡፡

# ጥናት ስድስት ኤፌ 4፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ጥሪው የመጣው ከእግዚአብሄር ዘንድ ነው፡፡ ጥሪው አስቀድመው በተቀበሉት ሰዎች በኩል የመጣ ሲሆን፤ በወንጌል ስብከት ነው ጥሪው ለሰዎች የሚደርሰው፡፡
2. ፍጹም ትህትና፣ ገርነት፣ ፍቅር፣ ትዕግሥት ናቸው፡፡ አንድነቱ የተጀመረው በክትስቶስ ኢየሱስ ሞት ነው፡፡
3. ትህትና፣ ገርነት፣ ፍቅርና ትዕግሥት በእያንዳንዱ አማኝ ህይወት በግልጽ የሚለማመዳቸው ነገሮች ከሆኑ ግለኝነት፣ እኔ እበልጥ ባይነት፣ እኔ ብቻ ልሰማና የመሳሰሉት በቅዱሳን መሃል ለመለያየት ምክንያት ሆነው የሚታዩት ነገሮች ሁሉ ሥፍራ አይገኙላቸውም ነበር ለማለት ይቻላል፡፡
4. አማኞችን አንድ የሚያደርጓቸው ሰባት ነገሮች አንድ ተስፋ፣ አንድ አካል፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ ጌታ፣ አንድ እምነት፣ አንድ ጥምቀትና አንድ አምላክ ናቸው፡፡ እግዚአብሄር ለአንድነት ትልቅ ሥፍራን የሚሰጥበት ምክንያት በመጀመሪያ ደረጃ ክርስቶስ የሞተው ሰውንና አምላክን አንድ ለማድረግ፤ ቀጥሎም ደግሞ ሰውንና ሰውን አንድ ለማድረግ በመሆኑ፤ መለያየት የሚለው ሃሳብ በአጠቃላይ በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ሃሳብ ነው፡፡
5. ‹‹ጸጋ›› ተሰጥቶናል፣ የጸጋውን መጠን የወሰነው ክርስቶስ ነው፣ ጸጋው የተሰጠው ለእያንዳንዳችን ማለትም ለሁላችንም ነው፡፡ አማኝ የሆነ ሁሉ ከክርስቶስ ኢየሱስ የጸጋን ስጦታ ያልተቀበለ እንደሌለ በድፍረት ለመናገር እንችላለን፡፡
6. ለቤተ ክርስትያን የተሰጡት ሐዋርያት፣ ነብያት፣ ወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይህ የሚያሳየኝ ነገር አንድ ሰው ሁሉንም አይነት ስጦታ እንደማይኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪ ደግሞ ሁሉም ሰው ስጦታው ተመሳሳይ ሳይሆን የተለያየ እንደሆነ ያለሁ፡፡
7. ክርስቶስ እነዚህን ሰዎች ለቤተ ክርስትያን የሰጠበት ዋነኛ ምክንያት ቁ12 እንደሚናገረው የክርስቶስን አካል ማለትም ቤተ ክርስትያን መገንባት ይቻል ዘንድ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ለማዘጋጀት ነው፡፡ በቁ13 እንደምናነበው ሁላችንም የእግዚአብሄርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኘው አንድነት በመምጣት ሙሉ ሰው በመሆን በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ድረስ ነው፡፡
8. በመጀመሪያ ደረጃ ቁ14 እንደሚያሳየን በትምህርት ነፋስ መፍገምገም አይኖርም፣ እውነትን በፍቅር መናገር እንለማመዳለን (ቁ15)፣ ወደ ክርስቶስ ማደግ ይኖራል (15)
9. በዚህ ቁጥር ላይ ቤተ ክርስትያን የተመሰለችው በአካል ነው፡፡ ቁ16 የሚነግረን አካል እንደሚገባ እንዲያድግና እንዲታነጽ ካስፈለገ እያንዳንዱ ብልት የሚጠበቅበትን ተሳትፎ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

# ጥናት ሰባት ኤፌ 4፡17-32 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አህዛብ በአስተሳሰባቸው ከንቱነት ነው የሚመላለሱት፣ ልባቸው የደነደነ ነው፣ አያስተውሉም፣ ልቦናቸው የጨለመ ነው፣ ከእግዚአብሄር ህይወት ተለይተዋል፣ የማይረካ ምኞት አላቸው፣ ለርኩሰት ተሰጥተዋል፣ የሚኖሩት እንዳሻቸው ነው፣ ራሳቸውን ቅጥ ለሌለው ብልግና አሳልፈው የሰጡ ናቸው፡፡ አማኞችን ጳውሎስ የሚመክረውና ዓደራ የሚለው እንደ አህዛብ እንዳይመላለሱ ነው፡፡
2. የአህዛብ አዕምሮ ወይም አስተሳሰብ ከንቱ ሲል፣ የክርስትያን አዕምሮ ደግሞ የተለወጠና የታደሰ አስተሳሰብን ሊያዳብር ያስፈልጋል (ሮሜ 12፡1-2)፣ እነርሱ ልባቸው የደነዘዘ ሲሆን የአማኝ ልብ ግን የክርስቶስ ልብ/አዕምሮ አለን ይላል 1ኛ ቆሮ 2፡16፤ ይህም ማለት የርህራሄ፣ የይቅርታ፣ የምህረት ልብ ማለት ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ህሊናቸው መደንዘዙ፣ አማኝ በምንም መንገድ ለጽድቅም ሆነ ለሃጥያት እንዳይደነዝዝ በጎ ህሊና ሊኖረው እንደሚገባ በ1ኛ ጢሞ 1፡19 ላይ ተነግሮታል፡፡
3. በዚህ ቁጥር ላየ እንደ አህዛብ ከንቱ ኑሮ እንዳይኖሩ ምክንያት አድርጎ የሚነግራቸው ነገር፣ ክርስቶስን ያወቁት በዚህ መንገድ እንዳልሆነ ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ሲላቸው በክርስቶስ ያለው ህይወት የተለየ እንደሆነና መንገዱ ከአህዛብ መንገድ የተለየ መሆኑን አውቃችሁና ተምራችሁ የተረዳችሁት ነገር ስለሆነ በቀድሞው አሮጌው ኑሯችሁ ልትኖሩ አትችሉም ማለቱ ነው፡፡
4. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የማያቸው ሁለት አይነት ሰዎችን ነው፡፡ አንደኛው አሮጌ ሰው በመባል የሚታወቅ ሲሆን (ቁ22)፤ ሁለተኛው ደግሞ አዲሱ ሰው በመባል ይታወቃል (ቁ24)፡፡ ጳውሎስ አሮጌው ሰው የሚለው ክርስቶስን ከማወቃችን በፊት የነበረውን ማንነታችንን ሲሆን፤ አዲሱ ሰው በማለት ሲናገር ደግሞ ክርስቶስን ካወቅን በኋላ ያለውን የተለወጠውን ማንነታችንን ማለቱ ነው፡፡
5. አሮጌው ሰውነታችን በሚያታልል ምኞቱ እንደጎደፈ እናነባለን፤ ስለዚህም ጳውሎስ ይህንን አሮጌውን ሰውነታችንን አውልቀን እንድንጥል ያዘናል፡፡ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተነገሩት አሮጌውን ሰውነታችንን አውልቀን እንድንጥል ያስፈለገባቸው ሁለቱ ምክንያቶች፡ አንደኛው በአዕምሯችን መንፈስ እንድንታደስ (ቁ23)፣ ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሄርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድንለብስ ነው (ቁ24)፡፡
6. ከቁ25 ጀምሮ እስከ ቁ32 ላይ አማኞች በህይወታቸው እንዲለማመዷቸው የተጻፉት ነገሮች ሁሉ ተፈጻሚነት ሊያገኙ የሚችሉት አሮጌው ሰው ሰልጥኖባቸው እያሉ ሊሆን እንደማይችል እውቅ ነው፤ በነዚህ ነገሮች ላይ ለመሰልጠን ካስፈለገ የአዕምሮ መታደስና አዲሱን ሰው መልበስ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡
7. መመሪያ የሰጠባቸው ሶስቱ ነገሮች ስለውሸት፣ ስለቁጣና ስለስርቆት ናቸው፡፡ ውሸትን እንዳንነጋገር ምክንያት አድርጎ ጳውሎስ የሰጠው የሁላችንንም የአንድ አካል ብልቶች መሆን ሲሆን፤ ይህንን ማለቱም ለወንድሞቻችንና ለእህቶቻችን ዋሸን ማለት ለራሳችን እንደምንዋሽ ይቆጠራል፣ ደግሞም ውሸቱ ያንን ሰው ብቻ ሳይሆን አካሉን ሁሉ የሚጎዳ ስለሚሆን ነው፡፡
8. ሌሎችን የሚያንጽና የሚጠቅም ነገር ከመናገር ይልቅ፤ የማይረባ ቃላትን ከአንደበታችን ማውጣት፣ መራር መሆን፣ ቁጣ፣ ንዴት፣ ጭቅጭቅ፣ ስድብ፣ ክፋትና ይቅር አለማለትን ሁሉ ያካትታል፡፡

"

# ጥናት ስምንት ኤፌ 5፡1-20 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በነዚህ ቁጥሮች መሰረት በፍቅር መመላለስ ማለት ልክ ክርስቶስ ለእኛ እንዳደረገው እኛም ለሌሎች ጥቅም ስንል አስፈላጊ የሆነውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን ማለት ነው፡፡ ለሌሎች ጥቅም የራስን ጥቅም መተውና ለሌሎች ሲሉ መጎዳት በጣም በጥቂቶች ህይወት የሚታይ ነገር ነው፤ ለዚህም ምክንያት የሚመስለኝ ትዕዛዙን ያለማወቅ ሳይሆን፣ ከራስ በላይ ነፋስ በሚለው የአለም አስተሳሰብ ስለተሞላንና ለአሮጌው ማንነታችን የመገዛታችን ምክንያት ይመስለኛል፡፡
2. የእግዚአብሄር ህዝብ በዚህ ክፍል ‹‹ቅዱስ›› የሚል መጠሪያ ነው የተሰጠው፡፡ ለዚህ ህዝብ የማይገቡ ተብለው በቁ3 ውስጥ የተነገሩት ነገሮች፤ ማንኛውም ዓይነት ዝሙት፣ ርኩሰትና፣ ስስት የሚሉት ናቸው፡፡ አጻያፊ ሆኖ የማናየው ከሶስቱ መሃል ስስትን (greed) ትክክለኛው ትርጉም ስግብግብነት የሚለው ነው፡፡
3. ከክርስትያን አንደበት መውጣት የሌለባቸውን ተገቢ እንዳልሆኑ አድርጎ የሚናገራቸው ነገሮች፡ የሚያሳፍርና ተራ ንግግር፣ ዋዛ፣ ፈዛዛ የመሰሉት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ግን መውጣት ያለበት ነገር ምስጋና ነው፡፡ ስስታም (greed) ለሚለው የተሰጠው ስም ‹‹ጣዖት አምላኪ›› የሚል ሲሆን፤ ይህ ከባድ ስም የተሰጠው ምክንያት እኔ እንደሚመስለኝ፤ የዚህ ሰው ልብ ለእግዚአብሄር ሊሰጠው የሚገባውን ትልቅ ፍቅር ለሌላ ነገር እንደ ገንዘብ ላለ ነገር በመስጠቱ ይመስለኛል፡፡
4. የሚያነጻጽርልን ሁለቱ ዘመኖቻችን፤ የቀድሞውን ዘመንና፣ የአሁኑን ዘመናችንን ነው፡፡ በሁለቱ ዘመኖች መሃል ያለው ልዩነት እጅግ ሰፊ ሲሆን፤ የልዩነቱንም ስፋት የሚያሳየን የብርሃንና የጨለማን ልዩነት በማሳየት ነው የነዚህንም ልዩነት የሚያስረዳን፡፡ በብርሃን የመመላለስ ፍሬ ሆነው የተነገሩት ነገሮች፡ በጎነት፣ ጽድቅና እውነት የሚሉት ናቸው፡፡
5. የጨለማ ሥራ ፍሬ እንደሌለው አድርጎ ነው የሚነግረን፡፡ የጨለማ ሥራ ፍሬ የለውም ሲል ምንም ዓይነት ፍሬ አያፈራም ማለት ሳይሆን፤ በተለይ የጌታ ልጆች ለሆኑት የሚጠቅም፣ የሚያንጽ ወይም ደግሞ እግዚአብሄር የሚከብርበትና ደስ የሚሰኝበት አይነት ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል ማሳየቱ ይመስለኛል፡፡
6. በነዚህ በሁለቱ መሃል ያለው ግንኙነት እንደምረዳው ከሆነ፤ እንደ ብርሃን ልጆች ለመመላለስ እግዚአብሄርን ደስ የሚያሰኘው ነገር ምን እንደሆነና የፈቃዱን ምንነት ማወቅ ይኖርብናል፤ ይህንንም ማግኘት የሚቻለው በቃሉ ውስጥ ነው፡፡ የጨለማን ሥራ መግለጥ የምንችለው የብርሃንን ሥራ በመሥራት ሰዎች ከጨለማው ሥራ ጋራ አነጻጽረው በማየት ትክክል እንዳልሆነ ማየት እንዲችሉ ብርሃን እናበራብታለን ማለት ነው፡፡
7. ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች የሚያስጠነቅቀው እንደ ጥበበኛ ሰው እንጂ ጥበብ እንደሌለው ሰው እንዳይመላለሱ ነው፡፡ ጥበበኛ ሰው የቀኖቹን ክፋት ተረድቶ ዘመኑን በመዋጀት ይመላለሳል፣ ጥበበኛ ሰው የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ ያስተውላል፣ ይመረምራል እንጂ በዘፈቀደ አይመላለስም፣ ጥበበኛ ሰው በመንፈስ እንጂ በወይን ጠጅ ራሱን አያሰክርም፤ ሞኝ ሰው ግን ኑሮውን የሚኖረው ጥበበኛው በሚኖረው ተቃራኒ ህይወት ነው፡፡
8. ይህ ክፍል እግዚአብሄርን እንድናመሰግነው የሚነግረን ስለሁሉ ነገር ሲሆን፤ የምናመሰግንበትንም ጊዜ ሲነግረን ‹‹ሁልጊዜ›› እንድናመሰግነው ነው የሚናገረው፡፡ እግዚአብሄርን የምናመሰግነው መልካም ነው ብለን የምናምናቸው ነገሮች በህይወታችን ሲበዙልንና በጤና፣ በጓደኛ፣ በንብረት ስንበለጥግ ብቻ ሳይሆን፤ ህይወት የማይመች ሲሆንና ጤንነት ሲጎድል፣ ኪስ ባዶ በሆነ ሰዓት ሁሉ እግዚአብሄር ሊመሰገን የሚገባው አምላክ መሆኑን ሲያሳስበን ይመስለኛል፡፡

# ጥናት ዘጠኝ ኤፌ 5፡21-6፡9 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል ጳውሎስ ሶስት ዓይነት ግንኙነቶች ላይ አተኩሮ ሲናገር ነው የምናየው፤ እነዚህም በባልና በሚስት መሃል ያለ ግንኙነት፣ በወላጅና በልጆች መሃል ያለ ግንኙነትና በአሰሪና በሰራተኛ ወይም በባሪያና በጌታ መሃል ያሉ ግንኙነቶች ናቸው፡፡
2. ለሁለቱም በጋራ የተሰጠው ትዕዛዝ በቁ21 ላይ የሰፈረው አንዳቸው ለሌላቸው እንዲገዙ ነው፡፡ ለሚስቶች በግል ተሰጥቶ የምናየው በቁ21 ላይ ያለው ለባሏ እንድትገዛ የሚለው ነገር ተደጋግሞ ተነግሯል፤ ሚስት ለባሏ የመገዛትን ነገር፤ ቤተ ክርስትያን ለክርስቶስ ከመገዛቷ ጋራ በማነጻጸር ነው የተናገረው፡፡ ክርስቶስ ቤተ ክርስትያንንን እንደወደዳት…ሚስቶቻችሁን ውደዱ›› የሚል ነው፡፡
3. ‹‹ክርስቶስ›› እና ‹‹ቤተ ክርስትያን›› የሚሉትን በቁ23፣ 24፣ 25፣ 27፣ 29፣ 30፣ 32 ላይ ማለትም ቢያንስ ሰባት ጊዜ እናገኛቸዋለን፡፡ ባልና ሚስትን በተመለከተ ጳውሎስ ለማስተማር በተነሳበት ክፍል ክርስቶስንና ቤተ ክርስትያንን ትልቅ ሥፍራ ሰጥቶ ሰባት ጊዜያት የጠቀሰበት ምክንያት፤ ክፍሉን ሁሉ ስንመለከት የክርስቶስና የቤተ ክርስትያን ግንኙነት በትዳር ውስጥ ሊኖር ለሚገባው ግንኙነት ሞዴልና ቁልፍ የሆነ ነገር በመሆኑ ነው፡፡
4. በዚህ ስፍራ ጥልቅ ምስጢር ሆኖ የተነገረው ነገር የሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋራ አንድ በመሆን ሁለቱም አንድ ሥጋ የመሆናቸው ነገር ነው፡፡ የባልና የሚስትን ሃላፊነት ጳውሎስ የጠቀለለው፤ ባል ሚስቱን እንራሱ አድርጎ እንዲወዳትና፤ ሚስት ደግሞ ባሏን እንድታከብር ነው፡፡
5. በዚህ ግንኙነት ውስጥ ልጆች ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙና አባትና እናታቸውን እንዲያከብሩ ሲሆን፤ አባቶች ደግሞ ልጆቻቸውን እንዳያስቆጡ፣ ነገር ግን በጌታ ምክርና ተግሳጽ እንዲያሳድጉ ነው፡፡ እነዚህ የጌታን ስም እያስገባ የተናገራቸው አነጋገሮች የሚጠቁሙን ልጆችም ሆኑ ወላጆች እግዚአብሄርን የሚፈሩና እርሱን ለመታዘዝ የሚኖሩ እንደሆኑ ማወቅ ይቻላል፡፡
6. ባሮች ለጌቶቻቸው በአክብሮት፣ በፍርሃትና በልበ ቅንነት ልክ ለጌታ የሱስ ክርስቶስ እንደሚታዘዙ ሆነው እንዲታዘዙላቸው ያዛቸዋል፤ ጌቶች ደግሞ ‹‹እናንተም ጌቶች ሆይ እንዲሁ አድርጉላቸው›› በማለት ተመሳሳይ ትዕዛዝን ይሰጣቸዋል፡፡ እንደሌሎቹም ግንኙነቶች ይህም ግንኙነት ክርስቶስ የሚፈልገውንና የሚወደውን ማድረግ ማእከላዊ ቦታ ተሰጥቶት እንመለከታለን፡፡
7. ከለጀ
8. ለባለትዳሮች ቁ22 ‹‹ለጌታ እንደምትገዙ›› ለቤተሰብ ኤፌ 6፡1 ‹‹በጌታ ታዘዙ››፣ በስራ ቦታ ኤፌ 6፡5 ‹‹ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ›› በማለት መናገሩ መመሪያዎቹ ያለመኑትንና የክርስቶስን ጌትነት ያልተቀበሉትን የማይመለከት እንደሆነ በግልጽ ይታያል፡፡ ይህ የሚመለከታቸው ለእርሱ ጌትነት ራሳችንን አስገዝተናል ብለው ለሚሉ ለአማኞች ብቻ ነው፡፡
9. በዚህ ቁጥር ላይ ማዕከላዊ ሥፍራ ተሰጥቶት የምናየው ክርስቶስን ነው፤ ይህንንም ማለት ያስቻለኝ ምክንያት እነዚህ ግንኙነት የሚያደርጉት ‹‹አንዳችሁ ለአንዳችሁ›› የተባሉት ሰዎች የሚያደርጉትን ማናቸውም ነገር ሊያደርጉ የሚገባበትን ምክንያት ሲነግራቸው ለክርስቶስ ካላቸው አክብሮታዊ ፍርሃት የተነሳ እንደሆነና በመሃላቸው ሌላ ሶስተኛ ሰው እንዳለ ሆነው እንጂ ለራሳቸው ደስታና ፍላጎት ብቻ እንደማይኖሩ ሲረዱ ግንኙነቱ ይሰምራል፡፡

## ጥናት አሥር ኤፌ 6፡10-24 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ክርስትያን የእግዚአብሄርን ሙሉ የጦር ዕቃ መልበስ የሚኖርበት የዲያቢሎስን የተንኮል ሥራ መቋቋም እንዲችል ነው፡፡ የጦር ዕቃዎቹ የእግዚአብሄር ተብለው የተጠሩበት ምክንያት፤ የጦር መሳሪያዎቹ ሁሉ ሰው ሰራሽ ስላልሆኑና ሊሰጠንና ልንቀበል የምንችለውም ከእግዚአብሄር ብቻ ስለሆነ ነው፡፡
2. ጳውሎስ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የክርስትና ህይወትን እንደ ጦር ሜዳ እንደሆነና ወደ ጦርነት እንደገባን ነው ሊያሳየን የሚሞክረው፡፡ ጦርነቱ መንፈሳዊ ሲሆን፤ ጦርነቱም ከስጋና ከደም ወይም ከሰው ጋራ ሳይሆን ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከሃይላት፣ እንዲሁም በሰማያዊ ሥፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ጋራ ነው፡፡
3. የእውነት ዝናር፣ የጽድቅ ጥሩር፣ የሰላም ወንጌል፣ የእምነት ጋሻ፣ የመዳን ራስ ቁርና የመንፈስ ሰይፍ ናቸው፡፡ ይህ መሳሪያ ከሌሎቹ እንድንለብስ ከተነገሩን ሁሉ የሚለየው፤ ሌሎቹ ሁሉ ከጠላት ለሚመጣው ነገር የመከላከያ መሳሪያዎች ሲሆኑ ይህ ግን ጠላትን የምናጠቃበት መሳሪያ ነው፡፡ ኢየሱስ ፈታኙን ዲያቢሎስ በተለያዩ ነገሮች ሲፈትነው በማቴ 4፡1-11 ‹‹ተብሎ ተጽፏል›› በማለት ቃሉን በመጠቀም ድል እንዳደረገው እንረዳለን፡፡ ከኢየሱስ እንደምናየው መሳሪያውን ለመጠቀም ቃሉን በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል፡፡
4. ከእግዚአብሄር ከተሰጡን የጦር ዕቃዎች መሃል ጀርባችንን ለመከለል የሚረዳን አይገኝበትም፤ ይህም የሆነበት ምክንያት እኔ እንደምረዳው ከሆነ ይህ ሽሽተን ወደኋላ የምንልበት ጦርነት ስላልሆና ሽንፈት እንደ አማራጭ ያልተሰጠበት በመሆኑ በጦርነቱ ወደፊት እየገፉ መሄድ እንጂ ወደኋላ ማፈግፈግ አማራጭ ስላልሆነ ነው ብዩ አስባለሁ፡፡
5. ‹‹ይህንን በማሰብ›› ሲል በጦርነት ላይ መሆናችንን ሁል ጊዜ የምናስበው ነገር መሆኑን ሲያሳስበን ነው፡፡ በጦርነት ላይ መሆናቸውን በማሰብም ማድረግ የሚገባቸው ሁለት ነገሮች፤ በመጀመሪያ ራሳቸው ሁልጊዜ የነቁና የተዘጋጁ እንዲሆኑ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ቅዱሳን ሁሉ በዚህ ጦርነት ውስጥ ስላሉ አንዳቸው ለሌላቸው እንዲጸልዩ ነው፡፡
6. ጳውሎስ እንዲጸለይለት ያቀረባቸው የጸሎት ርዕሶች፡ ወንጌልን ሲናገር በድፍረት መናገር እንዲችል፣ የሚናገረው ቃል እንዲሰጠውና፣ መናገር የሚገባውን በድፍረት እንዲናገር የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ አነጋገሮች የእግዚአብሄር አገልጋይ ከእግዚአብሄር ተቀብሎ የሚያስተላልፍ እንጂ የራሱን ሃሳብ ለሰዎች የሚያስተምር መሆን እንደማይገባው መረዳት ይኖርበታል፡፡
7. በነዚህ ክፍሎች ውስጥ ጳውሎስን በመላላክ የሚያገለግለው ወንድም ስም ቲኪቆስ ይባላል፡፡ ቲኪቆስ የተወደደ ወንድም፣ ታማኝ አገልጋይ፣ ከጳውሎስ ጋራ ክርስቶስን የሚያገለግል ሌሌ ተብሎም ተጠርቷል፡፡
8. ከዚህ ክፍል አንጻር ቅዱሳን በጸሎት መተጋገዛቸው እጅግ አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝበት ምክንያት ጦርነት ውስጥ ስለሆኑና ጠላት በተለያየ አቅጣጫ ኢየሱስ በዮሐ 10፡10 እንደተናገረው ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ስለሚመጣ እርስ በእርሳችን በጸሎት ለሌሎች መጋደል አማራጭ የሌለው ነገር ነው፡፡